የሰ/መ/ቁ. 20416

ታህሣሥ 08 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ ቢኒያም ገረመው - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የቻይና መንገድና ድልድይ ሥራ ድርጅት

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በደቡብ ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፎገራ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

አመልካች ተሻሽሎ በቀረበ የክስ ማመልከቻ ተጠሪ ከሥራ ያላግባብ ያሰናበታቸው ስለሆነ አዋጁ የሚፈቅድላቸውን ክፍያዎች እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበተው ከሕግ ውጭ በመሆኑ የስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ የአመት ፈቃድ በገንዘብ ተቀይሮ፣ እንዲሁም የካሣ ክፍያ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ በደቡብ ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም አመልካች ከስራ የተሠናበቱት በሕገ ወጥ መንገድ መሆኑን በመቀበል የሥር ፍ/ቤት ግን ክሱ እንዲሻሻል ሲያዝ በቂ ምክንያት ያልነበረው በመሆኑና የተጠየቀውን ገንዘብ ከፍ ለማድረግ ብቻ ክስ ሊሻሻል እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 ስላልተመለከተ አመልካች ክርክሩን ሊቀጥል የሚገባው መጀመሪያ ባቀረበው የገንዘብ መጠን ነው በማለት አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ክስ የጠየቁትን የአገልግሎት ክፍያና የ2 ወር ደመወዝ ብቻ እንዲከፍላቸው ወስኗል፡፡



የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ በማድረግ በመጀመሪያ በቀረበው ክስ መሠረት ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱተው ለሠበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ተጠሪ ለአቤቱታው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ልኳል፡፡ ነገር ግን ተጠሪው መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ችሎቱ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት ውሣኔ የሠጠው የአመልካችን የተሻሻለ ክስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግን አመልካች በመጀመሪያ ክሣቸው ላይ የጠየቁትን የገንዘብ መጠን ከፍ ለማድረግ ብቻ ክሱ እንዲሻሻል መደረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ክስ መሠረት አድርጎ ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ ይህ ችሎትም ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ለማድረግ የሕግ መሠረት ነበረው ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክቷል፡፡

የመጀመሪያው ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል የፈቀደበት ምክንያት በመጀመሪያው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ያልተመለከተ ቢሆንም ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል የተፈቀደው አመልካች የሚጠይቋቸውን መብቶች በተብራራ ሁኔታ አሻሽለው እንዲያቀርቡ መሆኑን በውሣኔው ላይ አስፍሯል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካቹ በቀድሞ ክሣቸው ከጠየቁት ዳኝነት በተጨማሪ በሕገ-ወጥ ስራ ስንብት ምክንያት ሊከፈሏቸው የሚገባቸውን ሌሎች መብቶች አካተው ጠይቀዋል፡፡ ይህም ቀድሞ እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የገንዘብ መጠን ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤትም የተሻሻለውን ክስ ውድቅ ያደረገው በክስ ማሻሻል ሠበብ በመጀመሪያ ዳኝነት የተጠየቀበትን የገንዘብ መጠን ከፍ ማድረግ አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 መሠረት ክስ ሲሻሻል ዳኝነት የተጠየቀበትን የገንዘብ መጠን ከፍ ማድረግ ይቻል ወይም አይቻል እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 91 መሠረት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ